በዚህ ስፍራ ሚስት አታግባ ሴቶች ልጆችም አይሁኑልህ	“እንግዲህ ስለ አሁኑ ችግር ይህ መልካም ይመስለኛል፤ ሰው እንዲህ ሆኖ ቢኖር መልካም ነው።” 1ኛ ቆሮንቶስ 7፥26
በክፉ ሞት ይሞታሉ	“ሬሳህ ለሰማይ ወፎች ሁሉ ለምድርም አራዊት መብል ይሆናል፥ የሚያስፈራቸውም የለም።” ዘዳግም 28፥26
ትበላና ትጠጣላችሁ ዘንድ ከእነርሱ ጋር ለመቀመጥ ወደ ግብጥ ቤትን አትግባ	“ወደ ግብጥ ቤት ከመሄድ ወደ ልቅሶ ቤት መሄድ ይሻላልና፤ እርሱ የሰው ሁሉ ፍጻሜ ነውና፥ ሕያውም የሆነ በልቡ ያኖረዋልና።" መክብብ 7፥2
የእስራኤል አምላክ እንዲህ ይላልና ከዓይናችሁ የእልልታን ድምጽ አስቀራለሁ	“የከበሮው ሐሤት ቀርቶአል፥ የደስተኞች ድምፅ ዝም ብሎአል፥ የመሰንቆ ደስታ ቀርቶአል።” ኢሳይያስ 24፥8
በደላችንስ ምንድነው?	“አሕዛብ ሁሉ፦ እግዚአብሔር በዚህች ምድር ስለ ምን እንደዚህ አደረገ? ዘዳግም 29፥24
ሕጌንም አልጠበቁም	ከአሕዛብም ጋር ተደባለቁ፥ ሥራቸውንም ተማሩ። ለጣዖቶቻቸውም ተገዙ፥ ወጥመድም ሆኑባቸው።መዝ 106:35-36
ምሕረትንም አላደርግላችሁም	“በዚያም የማያዩትን የማይሰሙትንም የማይበሉትንም የማያሸቱትንም፥ በሰው እጅ ከእንጨትና ከድንጋይ የተሠሩትን አማልክት ታመልካላችሁ።” ዘዳግም 4፥28
ዓይኔ በመንገዳችሁ ላይ ነው ከፊቴም አልተሰወሩም (16:17)	“እንዲገለጥ ባይሆን የተሰወረ የለምና፤ ወደ ግልጥ እንዲመጣ እንጂ የተሸሸገ የለም።” ማርቆስ 4፥22
በውኑ ሰው አማልክት ያልሆኑትን ለራሱ አማልክትን አድርጎ ይሠራልን?(16:20)	“ነገር ግን በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን ሳታውቁ በባሕርያቸው አማልክት ለማይሆኑ ባሪያዎች ሆናችሁ ተገዛችሁ፤” ገላትያ 4፥8
እጄንና ኃይሌን አስታውቃችኋለሁ፤	“እግዚአብሔርም ደግሞ ሙሴን አለው፦ ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ትላለህ፦ የአባቶቻችሁ አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ እግዚአብሔር ወደ እናንተ ላከኝ፤ ይህ ለዘላለሙ ስሜ ነው፥ እስከ ልጅ ልጅ ድረስም መታሰቢያዬ ይህ ነው።” ዘጸአት 3፥15
በመሠዊያቸው ቀንዶች ተቀርጾአል። — ኤርምያስ 17፥1	“ምነው በብረት ብርና በእርሳስ በዓለቱ ላይ ለዘላለም ቢቀረጽ!” — ኢዮብ 19፥24
“በምድረ በዳ እንዳለ ቍጥቋጦ ይሆናል፥ — ኤርምያስ 17፥6	“ምድርም በሁለንተናዋ ዲንና ጨው መቃጠልም እንደ ሆነባት፥ እንዳትዘራም እንዳታበቅልም፥ ማናቸውም ሣርና ልምላሜም እንዳይወጣባት፥ እግዚአብሔር በቁጣውና በመዓቱ እንደ ገለባበጣቸው እንደ ሰዶምና ገሞራ እንደ አዳማና እንደ ሲባዮ እንደ ሆነች ባዩ ጊዜ፥” — ዘዳግም 29፥23
“በእግዚአብሔር የታመነ እምነቱም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ቡሩክ	“የያዕቆብ አምላክ ረዳቱ የሆነ ተስፋውም በአምላኩ

ነው።” — ኤርምያስ 17፥7	በእግዚአብሔር የሆነ ሰው ምስጉን ነው፤” — *መዝሙር* 146፥5
“ያልወለዷትውን እንደምታቅፍ ቆቅ. — ኤርምያስ 17፥11	“እግዚአብሔር ግን፦ አንተ ሰነፍ፥ በዚች ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ሊወስዱአት ይፈልጓታል፤ ይህስ የሰበሰብኸው ለማን ይሆናል? አለው።” — ሉቃስ 12፥20
“አቤቱ፥ የእስራኤል ተስፋ ሆይ፥ የሚተዉህ ሁሉ ያፍራሉ. — ኤርምያስ 17፥13	“አቤቱ፥ ኃይልህን እዘዝ፤ አቤቱ፥ ይህንም ለእኛ የሠራኸውን አጽናው።” — *መዝሙር* 68፥28
“እነሆ፦ የእግዚአብሔር ቃል ወዴት አለች? አሁን ትምጣ ይሉኛል።” — ኤርምያስ 17፥15	“እርሱም፦ የመምጣቱ የተስፋ ቃል ወዴት ነው? አባቶች ከሞቱባት ጊዜ፥ ከፍጥረት መጀመሪያ ይዞ ሁሉ እንዳለ ይኖራልና ይላሉ።” — 2 ኛ ጴጥሮስ 3፥4
ለራሳችሁ ተጠንቀቁ. — ኤርምያስ 17፥21	“ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር አምላክህ ሰንበት ነውና፤ አንተ እንደምታርፍ ሎሌህና ገረድህ ያርፉ ዘንድ፥ አንተ ወንድ ልጅህም ሴት ልጅህም ሎሌህም ገረድህም በሬህም አህያህም ከብትህም ሁሉ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ።” — ዘዳግም 5፥14
" የኢየሩሳሌምንም አዳራሾች ትበላለች፥ አትጠፋም።” — ኤርምያስ 17፥27	“የእግዚአብሔርንም ቤትና የንጉሡን ቤት አቃጠለ፤ የኢየሩሳሌምንም ቤቶች ሁሉ፥ ታላላቆቹን ቤቶች ሁሉ፥ በእሳት አቃጠለ።” — 2 ኛ ነገሥት 25፥9
“ እነሆ፥ ጭቃው በሸክላ ሠሪ እጅ እንዳለ፥ እንዲሁ እናንተ በእኔ እጅ አላችሁ።” — ኤርምያስ 18፥6	“ነገር ግን፥ አንተ ሰው ሆይ፥ ለእግዚአብሔር የምትመልስ ማን ነህ? ሥራ ሠሪውን፦ ስለ ምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ይለዋልን?” — ሮሜ 9፥20
ካሰብሁት ክፉ ነገር እጸጸታለሁ።ኤርምያስ 18:8	“እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፋት ራራ።” — ዘጸአት 32፥14
እነሆ፥ ክፉ ነገር እፈጥርባችኋለሁ. — ኤርምያስ 18፥11	“እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ የይሁዳ ንጉሥ እንዳነበበው እንደ መጽሐፉ ቃል ሁሉ በዚህ ስፍራና በሚኖሩበት ላይ ክፉ ነገር አመጣለሁ።”

	— 2ኛ ነገሥት 22፥16
“በጠላት ፊት እንደ ምሥራቅ ነፋስ እበትናቸዋለሁ" — ኤርምያስ 18፥17	“ወደ ቤቱ ዳግመኛ አይመለስም፥ ስፍራውም ዳግመኛ አያውቀውም።” — ኢዮብ 7፥10
“ለነፍሴ ጕድጓድ ቈፍረዋልና" — ኤርምያስ 18፥20	“በከንቱ ያጠፉኝ ዘንድ ወጥመዳቸውን ሸሽገውብኛልና፥ ነፍሴን በከንቱ አበሳጭተዋልና።” — መዝሙር 35፥7
“ሚስቶቻቸውም የወላድ መካንና መበለቶች ይሁኑ. — ኤርምያስ 18፥21	“ለሰይፍ እጅ አልፈው ይሰጣሉ፥ የቀበሮም እድል ፈንታ ይሆናሉ።” — መዝሙር 63፥10